# ወ ፈ ፍ ታ

## አጭር ልቦለድ

ዓለማየሁ ታዬ

alalemayehu@yahoo.com

ጎጆዪቱ በሙቀትዋ ጎረቤቶቿን አቅፋለች፡፡ ማዕዘን ላይ በበሬ ቆዳ ተለጉሞ በጠፍር ግጥም ተደርጎ የታሰረ አቧራ የጠጣ አገልግል ተሰቅሏል፡፡

በሻ አጎናፍር ፍዝዝ ብለው አገልግሎን ሲያዩ ቆዩና እይታቸውን ወደ ውጭ አሻገሩ፡ - ንፋስ የለም፣ መብረቅ የለም. በአንድ የሙዚቃ ስልት ዝም ብሎ ያላዝናል፡፡

“እንግዲህ ድሮ የሆነ ታሪክ ነው፡፡”
“እሺ!” ተባለ፡፡ ያሮጊትዋን አልጋ የከበቡት ማደርተኞች
የዝናቡን ማብራት በሽማግሌው ወግ ለማጠበቅ ቆሎአቸውን እየቆረጣጠሙ ተመቻቹ፡፡
አሮጌትዋም እማማ አረጋሽ ብርድ የቆፈነነውን እግራቸውን በጋቢያቸው ውስጥ አጥፈው ሞጭሟጭ አይናቸውን አጎታቸው ላይ ተከሉ፡፡

“ሴትዬዋ አንድ ያልታሰበ ዕለት ቁ! ቁ! ብላ ጮኸች፡፡ ፀጉሯን እየነጨች ደረቷን እየደለቀች፡፡ ሰዉ ከየቤቱ እየበረገገ እየተመመ መጣ ደረሰና
“ምን ሆንሽ?” ተባለች፡፡ ”ምን ተፈጠረ? ማን ተቀበረ?”

“ወይኔ! ወይኔ ወርቄን! ወይኔ! ወርቄን!” “እያለች እዬዬዋን አስነካችው”

“እረ ያዟት ፀጉሯን ነጭታ ልትጨርስ ነው፡፡! ”

“እንዴ ምንድን ነው ጉዱ? ተደብድባ ነው ወይስ.....”
“ያዟትና ጠይቋት እንጂ.! ተዘረፈች ወይስ ምን ሆነች?”
“ምን ሆንሻል እቱ ምን ነካሽ የኔ ትርንጎ! ” አሏት ጉረቤትዋ እማማ ዘነቡ፡፡
“ምን ያልሆንኩት አለ! ኑ ጉዴን እዩ፡፡ ወይኔ ወርቄን! ወርቄን!”

እያለች ወሬ አዳናቂ ነገር አዳማቂውን እየመራች ወደ ቤትዋ በር ተጠጋች፡፡ ጥርቅም ተደርጎ በተዘረጋው በሯ ጉበን ቀዳዳ አንገቷን አስግጋ ወደ ውስጥ ተመለከተችና እየጮኸች እያለቀሰች ወዲያ ስትሸሽ.... የሰዉ አይን የሸረሪት ድር የተበተበው በር ላይ እየተንቀዋለለ፡፡

"ምንድን ነው ነገሩ?"

"ሌባ እንዳይሆን?"

"እባብ ምናምን እንደሆነስ?"

"እንዴ.! ወርቄን ኮ ነው የምትለው.!" ሲባባሉ አሁንም

እማማ ዘነቡ፡ -

"ወንዶቹ ግቡና እዩላት እንጂ./ ብለው ቀጭን ትዕዛዝ አስተላለፉ በዚህ ጊዜ ወንዶቹ እርስ በርሳቸው እየተያዩ ሲያመነታቱ የዕድር ጥሩምባ ነፊው ተኮላ ፈንጠር ብሎ ፈጠን ፈጠን እያለ ወደ በሩ ተጠጋና ያልተቆለፈ ግን የተዘጋውን በር አንዴ በወታደር ጫማው በለው ጊዜ በሩ ሲጠጠጠጥ ብሎ ብርግድ አለ። ከ ጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተከላ ባዶ እጁን እያራገፈ:-

"ምንም ነገር የለም፡፡ ሰላም ነው፡፡ ሁለቱንም ክፍል ሳጥን ከፍቼ አጎዛ አንስቼ በርብሬአለሁ፡፡" ብሎ ትርንጎ ላይ ጥቃቅን ጠዮቂ ዐይኖቹን ሲያፈጥ እም አእላፍ አይኖች ተከተሉት...

የለበሰችው ሙ ሉ ቀሚ ስ በጥቁር ጥለት ወገቡ ላይ ሸብ አድርጎአል እግርዋ ይንቀጠቀጣል ጣቶችዋን እንቅፋት ተረከዝዋን ንቃቃት በልቷታል፡

" □እረ አለ!" አለች አፏን ሸርመም አርጋ አንገትዋን ወደ በሩ እየገፋች

"የት? "

"እውስጥ ነዋ./ ተንጠልጥሏል፡፡"

"ምኑ?"

"አገልግሉ፡፡" ጥፍሮችዋን እየቀያየረች ቆሎ ቆሎ ትበላለች፡፡ ዐይኖቿ ጎድጓዳቸው ውስጥ በፍርሃት ይንጨለጨላሉ፡፡

"ምን ሆነ አገልግሉ?"

"እዛ ውስጥ ነው ያለው ስላችሁ!" ብላ አየሩን በሁለት እጇዋ ወደ በሩ ቀዘፈችው፡፡ ወደ ኋላዋም አጣምራ ቀስ እያለች እየተንጎራደደች

“ወይኔ ወርቄን.! ጌጤን./መከሪያዬን./” እያለች አነባችና

“የናቴ እጅ አምሮኝ ወርቅነህን ሰነፍ ቶሎ አምጣልኝ ብዬ አገር ቤት አገልግል አስይዤ ብልከው ደመኞቻችን እመንገድ አገኙትና ህእ.!ህእ.!...” አለችና እምባዋ ማዲያት በጠበሰው ፊትዋ ላይ መንታ ሆኖ እያወረደ .... “አንገቱን ቆርጠው ባለቤቴን በገዛ አገልግሌ ጠፍረው ላኩልኝ.!” ከሚለቷ ስብሰባው በመቅጠጥ፣ በአግራሞት፣ በከንፈር ማጠባ ደምፅ ታመሰ፡፡ ጎረቤትዋ እማማ ዘነቡም ይህን እንደሰሙ ፊታቸው ወደ ግቢ ገብርኤል መለሱ...

“ታዲያ ምን ይሻላል ጎበዝ.!”

“ይወጣኣ.!ይከፈት አገልግሉ፡፡”

ተኮላ እግሩን እየጎተተ ቀስ እያለ ወደ ቤትዋ ዘለቀና አቧራ የጠጣች በበሬ ቆዳ ተለጉማ በጠፍር ግጥም ተደርጋ የተጠፈረች አገልግል ይዞ ወጣና ሰው መሀል ቀጭ አደረጋት፡፡

ማነ ይክፈታት ??

ወንዶቹ ፊታቸውን አኮፍትረው ሴቶች በነጠላቸው፣ በሹራባቸው አፋቸውን እየሸፈኑ ብዙ አይኖች አገልግልዋ ላይ.....

አሉና ባሻ አጎናፍር ወሬውን እንደጨረሱ ነገር ወደ መዳፋቸውን ሰደው የቅርጫ ጠረጴዛ ላይ ከተቀመጠው ነጭ የቆርቆሮ ሳህን ሽምብራ ቆሎ ዘግኑ፡፡ እየቆረጠሙ በአይናቸው ዙሪያ ገቡን አዳረሱት፡፡ የመቅሚቱ ጉጉት የያዛቸው መንደርተኞች ሁሉ ነገራቸው ጆሮ ሆኗል፡፡ አሮጊቷ ፍርሃት የረበበበት ፊታቸውን ከሚዘን ወደ ባሻ አጎናፍር መለሱና

“ካዛስ?” አሉ፡፡ “አገልግሎት ተከፈተ?”

...... ሲከፈት ላለሞየት ትርንጎ ከወደ መሃል ሸሸችና ወዲያ በረረች፡፡ አዳሜ አይኖቹን አገልግሉ ላይ ሰፍቶ እሷን ነገሬም ያላት አልነበር፡፡ አገልግሉም ተከፈተ ወስጡ የተገኘው ግን አንገቱ የተቆረጠ ጡቱ የተሸረፈ አሮጌ ጀበና የወዳደቁ ፒራሚድ የመቅሉ ልቃቂቶችን በጥላሸቱ ነካክቷቸዋል፡፡ አይኑን ማመን አቅቶት ሕዝቡ በመደነቅ እያመመ

ፊቱን ወዲህ ቢያዞር፣ - እማማ ዘነቡ ሚጅራታቸውን እያዳቀሩ ወደ ግቢ ገብርኤል አፍጥጠው ሃወልት ሆነው ቀርተዋል፡፡

“ምንድነ ነው ነገሩ?” ተባለ፡፡ “ይናገሩ ንጂ.!”

ብንን ብለው እወይ ልጄን.! አሉ እማማ ዘነቡ አይበሉባቸውን በእንባቸው እያረጠቡ፡ -

“ተነክታለች ማለት ነው.!” ባለቤቷ እኮ ከጠፉ ለታህሳስ ገብሬል አስር ዓመቱ፡፡ አሉና ደረታቸውን እየመቱ አይናቸውን እያበሱ ፊታቸውን ወደ ቤታቸው መለሱ....

“ከዚያስ?” አለች ያሮጊቷ አንዷ ጎረቤት

“ትርንጎ ምን ሆነች?” አለች ሌላዋ

“በዚያው ቀረቻ.! አበደቻ.! ወፈፈቻ! ምን ታርግ ልጄ፡ - ቤትዋን ፈርታ፡፡ አገልግልዋን ፈርታ፡፡ ደመኞቿን ፈርታ፡፡ አሉና እግራቸውን -ሊያፋታቱ ባሻ አጎናፍር ብድግ ሰሉ፡ - ጠያቂዎቹም ዝናቡ ማብራቱን ተመልከተው

“እግዚሃር ይማርዎ.!”

“ቀላሉን ያርግልዎ.!” እያሉ አራቱም ወደ የቤታቸው ተበታተኑ፡፡

“ባሻ አጎናፍር በቁማቸው”

“በይ ደህና እደሪ.! “ሲሏቸው፡ - እግራቸውን ብርድ ቆፍንኗቸው አሟቸው” የተኙት አሮጊት ፍንጥር ብለው ተነሱና ጎራዳቸውን በመቀነታቸው ተናፍጠው ወገባቸውን ሸብ እያደረጉ፡ -

“ይበሉ ይዘወልኝ ይሂዱ.!”

“ምኑን? አሉ ባሻ ጢም የዋጠውን ረዥም ፊታቸውን ወደ አሮጊትዋ እየመለሱ፡ -”

“እርሶ ደሮስ ስንት የሚወራ ጥሩ ወግ እያለ እ.! አሁን ብቻ ይዘወልኝ ይሂዱ” ብለው ጣታቸውን ወደ ሚዐዘን ቀሠሯት

አጎትየወም አገልግሉን እያዩ፡ -

“ምነው አረግዬ ፈራሽ እንዴ?” “አሏቸው ለፈነዳ የደረሰ ሳቃቸውን ወጠው፡ - ባይናቸውም እያባበሏቸው፡ -

“አይዞሽ አረግዬ አይዞሽ”.! ሲሏቸው

“ይዘወልኝ ይሂዱ ብያለሁ ይዘወልኝ ይሂዱ..”